# የዴሞክራሲ ስርዓቱ ስር እንዲሰድ…

**ከሃብሮማይ**

ghabrom@yahoo.com

የአገራችን ሁኔታ ስንቃኝ፣ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ማየትና ነገ መሆን ያለበትን ደግሞ ካለው የአከባቢው ነባራዊ ሁኔታ በማየት መተንበይ የግድ ይላል፡፡አንድ ነገር ይሆናል ወይም አይሆንም የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አሁን ካለበት ተጨባጥ ሁኔታ መነሳት ይኖርብናል፡፡አሁን ያለውን ሳንገነዘብ፣ሳናስተውልና ሳንመዝን ሰለ ነገ በጭፍን እንድንጓዝ ያደርገናል፡፡

ስለመጪው ምርጫ 2002 ስናስብ ካለፈው የ 97 ምርጫ ትምህርት ተወስዶ፣ በዛን ጊዜ የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች በማጤን፣ ጠንካራውን በበለጠ እንዲጎለብት በማድረግ፣ ደካማውን ደግሞ እንዳይደገም አሽቀንጥሮ በመጣል፣ መጪውን ምርጫ ከማንም ጊዜ በተሻለ ሰላማዊ ፣ፍትሃዊ፣ታማኝና ነፃ እንዲሆን ጥረት መደረግ እንዳለበት እሙን ነው፡፡

ምርጫውን ነጻ፣ሰላማዊና ፍትሃዊ ብሎም ታማኝ ለማድረግ፣ በሕገ መንግስቱ መሰረት ከማንም አካል ነጻ የሆነ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሟል፡፡የምርጫ ቦርድ አካላት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓረቲ ወገንተኝነት ነጻ ናቸው፡፡ የ 2002 የምርጫ ቦርድ በ 1997 ምርጫ ከተቋቋመው የምርጫ ቦርድ ለየት የሚያደርገው፣ በሕገ መንግስቱ መሰረት የምርጫ ቦርዱ አባላት የመጠቆም ስልጣን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠ ቢሆንም፣ ሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች ነፃ ናቸው የሚሏቸውን ግለሰቦች እንዲጠቁሙ መደረጉና የጠቆሟቸው ግለሰቦችም በቦርዱ አባላት ውስጥ መካተታቸው ነው፡፡ይህ እርምጃ የተወሰደው መጪው 2002 ምርጫ ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ ፍትሃዊ፣ነፃ፣ግልፅና ታማኝነት ያለው ምርጫ ለማድረግ መንግስት ካለው ቁርጠኝነት የመነጨ ይመስለኛል፡፡መንግስት ምርጫውን የተሻለ ለማድረግ ግማሽ መንገድ ተጉዞ ሌሎች ፓርቲዎች ምርጫውን ሰላማዊ እንዲሆን ጥረት

ማድረግ እንዳለባቸው እያሳየ ነው፡፡ይህ በመንግስት በኩል ያየነው መልካም ጅምር ነው፡፡

በተጨማሪም ገዢው ፓርቲም ምርጫውን ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ተአማኒነት ያለው እንዲሆን በፓርቲው ጋባዥነት በስነምግባር ደምብ ዙርያ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ድርድር እያካሄደ መሆኑ ይታወቃል፡፡ይህን ፓርቲው መጪው ምርጫ ከምን ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ፍትሃዊና ታማኝ እያደረገው ያለ እንቅስቃሴ አጠናክሮ መቀጠል አለበት እላለሁ፡፡ይህ በስነምግባር ደምብ ዙርያ የሚደረግ ውይይት በዋናኘት ፓርቲዎቹ በምርጫ ወቅት ሲንቀሳቀሱ ሊከተሉት በሚገባቸው ነጥቦች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ውይይቱ አገራችን የጀመረችውን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

መጪው ምርጫ ፍትሃዊና ሰላማዊ እንዲሆን፣ ምርጫ ቦርዱና ገዢው ፓርቲ ብቻ መንቀሳቀሳቸው በቂ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችም መጪው ምርጫ በሁሉም መለኪያ ነፃ፣ፍትሃዊና ታማኝ ለማድረግ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡በምርጫ 97 የነበረውን ሁከትና ብጥብጥ እንዳይደገም ያለፉ ስህተቶቻቸውን አርመው፣ የህዝባችን ሉዓላዊነት በሚገለጽበት ምርጫ ላይ፣ አገራዊ አጀንዳ ይዘው በጨዋታው ሕግ ብቻ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ተገንዝበው መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን ከ 97 ምርጫ በኋላ የተማሩት ነገር ምንድነው? የነበራቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይተው ምርጫውን በሁሉ መለኪያ ሰላማዊ፣ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊና ታማኝ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ ናቸውን? የሚለውን መገምገሙ ተገቢና ትክክል ይመስለኛል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን አብዛኛዎቹ ከምርጫ 97 ወዲህ ስለ አገሪቷ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና አጀንዳ ቀርፀው የተንቀሳቀሱበት አጋጣሚ የለም፡፡አብዛኛዎቹ ትኩረት አድርገው የነበሩት አገራዊ አጀንዳ ላይ ሳይሆን

ግለሰባዊ ክብር ላይ ነው፡፡እንዳንዴ "ተቋሞች የዴሞክራሲያችን ዋነኛ መገለጫዎች ናቸው" የሚለውን መርህ ወደኋላ በማድረግ "አንድ ግለሰብ ከሌለ ተቋሙ ይፈርሳል" የሚል አመለካከትና እምነት መያዛቸው ፓርቲዎቹ እንደ ተቋም በመርህና በሕግ የመገዛት ሳይሆን በአንድ ሁለት ግለሰቦች ክብር ላይ ማተኮር የተመሰረቱ እንደሆኑ ካለፈው አራት ዓመት አካሄዳቸው ያለተማረ ሰው አለ ብዬ አላምንም፡፡

ሁለተኛ የአገራችን ተቃዋሚዎች ከምርጫ 97 በኋላ አብዛኛዎቹ እርስ በርስ ሲፋጩና ሲበታተኑ፣ እንደገና ሲሰባሰቡና ሲሞጋገሱ ቆይቶም ሲበታተኑ፣ እንዳንዴማ መቼ ተፈረካክሰው መቼ እንደተጠገኑ ግራ እስከሚገባን ድረስ ፍጥነት ባለው አኳኋን በዚህ አዙሪት ውስጥ ተጠምደው እናስተውላቸዋለን፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች ዓላማቸውን፣ፖሊሲያቸውንና ስትራተጂያቸውን ለህብረተሰቡ በሚገባ ቢያስታውቁስ ጥሩ ነበር፡፡ህዝቡም የሚመጥናቸውን መልስ የሚሰጥበት ዕድል ያገኝ ነበር፡፡እነዚህ ፓርቲዎች ግን አብዛኛዎቹ በአንድ ሁለት ግለቸቦች አመለካከት የተዋቀሩና፣ ከአገር ይልቅ የራሳቸውን ክብር የሚያስቀድሙ ትንሽ ከተነኩ የሚበታተኑ መሰረት የሌላቸው ዓይነት እንደሆኑ መገንዘብ ችያለሁ፡፡

ስትራተጂካዊ ራእይ የሌለው ፓርቲ ከሆነ ጭፍን ተቃዋሚ ፓርቲ ስለሚሆን፣ ምንም እንኳ በህጉ መሰረት ፓርቲ የመመስረት መብት ቢኖረውም ለህብረተሰቡ የሚያመጣው ፋይዳ ግን የለውም - ከስሜታዊነት ከዚያም አልፎ ከሁከትና ብጥብጥ ውጪ፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የላቸውም፡፡ በአመራር ደረጃ እንኳን በሚያደርጉት ስብሰባ ሲሰዳደቡ፣ሲዘላለፉና የመደማመጥና የመቻቻል ባህል ድምጥምጡን ሲያጠፉት ነው የሚስተዋሉት፡፡እነዚህ ፓርቲዎች ልዩነትን እንደ ጌጥ ከማየት ይልቅ፣ በመሰዳደብና በመናቆር ሊፈቱት ከሞከሩ፣ የብዙ ብሄር፣ብሄረሰቦች፣ሃይማኖቶች፣ ባህሎች፣ቋንቋዎች፣ወጎች…ወዘተ ባለቤት ለሆነችና የተለያዩ ፍላጎቶች ያሉባት አገር፣ በሰለጠነ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ እንዴት ሊመሯት ይችላሉ?

ባሳለፍነው አራት ዓመት፣ ውስጥ እነዚህ ፓርቲዎች በአገሪቷ የዕድገት አጀንዳ ላይ ሳይሆን በውስጣቸው ያለውን ያልፀዳ አመለካከት ሲያፋጫቸው ነው የከረሙት፡፡የሚያሰዝነው ደግሞ ንትርኩ በአገራዊ አጀንዳ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ነው፡፡አብዛኛውን ስለ ግለ ክብራቸው የሚያጠነጥን ንትርክ መሆኑ በጣም የሚከነክን ነው፡፡ተቃዋሚ ነን ባይ ፓርቲዎች ከህዝብ ጥቅም ይልቅ ለግለሰብ ገናና ስም ሲማስኑ ይስተዋላሉ፡፡

ስለሆነም ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን ለመጪው ምርጫ 2002 በቂ ዝግጅት አድርገዋል ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለኛል፡፡እነሱ በቂ ዝግጅት አድረገናል ለማለት ቢሞክሩ እንኳ፣ ከምርጫ 97 በኋላ በምን ስራ ላይ ተጠምደው እንደነበሩ ህዝቡ በሚገባ ያውቀዋልና!

በቂ ዝግጅት ባለማድረጋቸውና በ2002 ምርጫ ለመሳተፍ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ሁለት ነገሮችን ይዞ እንደሚመጣ አያጠያይቅም፡፡አንደኛውና ጥሩ ነገር ተብሎ የሚታሰበው ምርጫ ላይ ተሳትፈው አሸናፊ ለመሆን ለመወዳደር መወሰናቸው ነው፡፡ምክንያቱም ህብረተሰቡ የተሻለ አማራጭ እንዲኖረው በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላለው፡፡ሁለተኛውና ዋነኛው ስጋት ግን እነዚህ ተቃዋሚዎች ለምርጫ በቂ ዝግጅት ባለማድረጋቸውና፣ በሃገራዊ አጀንዳ ላይ ተመስርተው ሳይሆን በጥቃቅን የጓዳ ችግራቸው ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው፣ ከዚያም አልፎ ገዢው ፓርቲ ለምርጫ በቂ ዝግጅት ስላደረገ መሸነፋችን አይቀሬ ነው የሚል አስተሳሰብ መያዛቸው ስለማይቀር ምርጫውን ፍትሃዊ፣ሰላማዊ ነፃና ታማኝ ምርጫ እንዳይሆን በስሜታዊ አካሄድ ላይ የተመሰረተ መርህና የፀረ ዴሞክራሲያዊ መንገድ  የመከተል አዝማምያ የሚኖላ ይመስለኛል፡፡እዚህ ላይ ፓርቲዎች ሊረዱት የሚገባ ነገር ሁሌም ውድድር ካለ መሸነፍም ማሸነፍም እንዳለ ሊያውቁ ይገባል፡፡ሽንፈትንም በፀጋ ተቀብሎ በሚቀጥለው ምርጫ የቤት ስራን ጠንክሮ መስራት ብልህነት ነው፡፡

ህዝብን እወክላለሁ ከሚል ፓርቲ ስሜታዊነት የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል በቅርቡ በገዢው ፓርቲ ጋባዥነት፣ ከተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች

በስነምግባር ደምብ ላይ ውይይይት እየተካሄደ መሆኑን ሰምተናል፡፡በዚህ ውይይት፣ “መድረክ” የተባለው ተቃዋሚ ፓርቲ፣ እኔ የምደራደረው ከገዢው ፓርቲ ጋር ብቻ ነው  ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች አልደራደርም ማለቱ ይታወሳል፡፡ለምን ቢባልም ከእገሌ ፓርቲ ጋር ፀብና ቁርሾ አለኝ ነው መልሱ፡፡ዴሞክራሲ ማለት በመሰረቱ አንድ ወጥ አስተሳሰብ የሚያስተናግድ ንድፈ ሃሳብ ሳይሆን፣  የተለያዩ ሃሳቦች የሚፋጩበት ስርዓት እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ይሁን እንጂ መድረኮች ይህ የገባቸው አይመስለኝም፡፡ይህ ደግሞ በመሰረቱ ፀረ ዴሞክራሲ ነው፡፡መድረክ ለምንድነው ውይይቱ ያልፈለገው? ከተባለ  በቂ የምርጫ ዝግጅት ባለማድረጉ፣ ተራ ነገሮችን እያነሳ መጪውን ምርጫ በተፈለገው መንገድ እንዳይሄድ ካለው ድብቅ ፍላጎት ይመስለኛል፡፡

ከምርጫ ወዲህ ተቃዋሚዎች የፖለቲካ ምህዳር ስፋትና መጥበብ የሚለኩት የነበሩ ከህዝቦች ተሳትፎ አኳያ ሳይሆን፣ የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ ካላቸው ጣልቃ ገብነት አንፃር እየተረጎሙ፣ የአገራችን ሉዓላዊነት ባለቤት በሆነው ህዝብ ላይ እየተቀለደ አልፏል፡፡በቅርቡ አንድነትን የመሰሉ የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝ የኔዘርላንድ ኤምባሲ በመሄድ እኛ እገሌ ከሚባል ፓርቲ ጋር አንወያይም ማለታቸው ይታወሳል፡፡በገዢው ፓርቲ ጋባዥነት በስነምግባር ደምብ ላይ በመካሄድ ያለው ውይይትም መድረክ ይሄንኑ ነው የደገመው፡፡ስለሆነም የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች የዴሞክራሲ ንድፈ ሃሳብ ያልገባቸውና ከመርህ ውጭ እንዳሻቸው እየሆኑ ያሉ ፓርቲዎች ናቸው ብል ከሚያደርጉት ያሉት እንቅስቃሴ አንፃር ያጋነንኩ አይመስለኝም፡፡

በአጠቃላይ የኛ አገር የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ግልፅ የሆነ (አንዳንዱ ጭራሽ ያለመኖር) የፖለቲካ ፕሮግራም አለመያዝ፣ ሽንፈትን በፀጋ አለመቀበል፣ የመቻቻል አቅም ማጣት፣ አደገኛ የፕሮፓጋንዳና የኮሚዩኒኬሽን ስልት፤ሂስና ነቀፌታ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣ ልዩነትን ወደ ጥላቻ መቀየር፣ አባልን በዓላማ ከማሰባሰብ ይልቅ በስሜትና ባልተጨበጠ መረጃ ማቅረብና ማራቅ፣

በገንዘብ ዙሪያ ምግባረ ብልሹነት፣ እርስ በርስ መወነጃጀል ወዘተ. መለያቸው እየሆነ መጥቷል፡፡

ገዢው ፓርቲ ምርጫው በሁሉም መለኪያ የተሻለ ለማድረግ የሚያሳየው ያለው ቁርጠኝነት ሊመሰገን ይገባል፡፡ይሁን እንጂ ጥረቱ በዚህ ብቻ መቆም እንደሌለበት ማወቅ ይኖርበታል፡፡አራት ዓመት ሙሉ ለምርጫ ምንም ዝግጅት ሳያደርጉ የቆዩ ፓርቲዎች፣ አሁን እንደጀመሩት የተለያዩ እንቅፋቶች ሊፈጥሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡በተጨማሪም በምርጫ ዋዜማ ብልጭ ብለው በምርጫ መጨረሻ ድርግም የሚሉ ፓርቲዎች ሲጨመሩባቸው፣ በመርህ ሳይሆን በስሜት የመሄድ አዝማምያው ጎልቶ የሚወጣበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡መንግስት የአገርንና የህዝብን ሰላም የማስጠበቅ ሃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ፣በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድ ለለውን ቅጥ ያጣ እንቅስቃሴ ችላ ሊለው አይገባም፡፡

ስለሆነም ገዢው ፓርቲ ከወዲሁ ይህ እንደሚመጣ ተገንዝቦ ምርጫውን ፍትሃዊ፣ ሰላማዊ፣ ነፃና ታማኝ እንዲሆን እያደረገ ያለውን ጥረት የበለጠ ትኩረት ሰጥቶት ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡በመንግስት ደረጃም መንግስት ሆደ ሰፊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ምርጫውን ሰላማዊ እንዳይሆን በሚጥሩ ፓርቲዎች ሃላፊነት በተሞላበት ደረጃ ወደ ሰላማዊ መድረክ እንዲቀላቀሉ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ምክንያቱም ምርጫውን ሰላማዊ፣ፍትሃዊ፣ነፃና ታማኝ የማድረግ ጉዳይ ይዘነው ያለን የዴሞክራሲ ሂደት ስር እንዲሰድ የሚያደርግ ትልቅ ጉዳይ ስለሆነ፡፡ሰላም!